ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ<br>ዙልሒጃ 29/1440 ሂ.
አውቃፍ ሚኒስትር<br>ኦገሰት 30/2019 ግ.

# በአለፈውና ባለንበት ዘመን የስደት ግንዛቤ

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**{إِلَّا تَنْصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللَّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُوا ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لَا تَحْزَنْ إِنَّ اللَّهَ مَعَنَا فَأَنْزَلَ اللَّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُوا السُّفْلَى وَكَلِمَةُ اللَّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَاللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ}**

ለአለው የዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም ((ነቢዩን) ባትረዱት እነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፡፡ የአላህም ቃል እርሷ ከፍተኛ ናት፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ነብያችን ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

መካ ውስጥ በነብዩ (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ላይ የሚደርሰው ስቃይ እጅጉን በበረታ ጊዜ ነብያችን በተላኩ በአመወስተኛው ዓመት ወደሐበሻ ምድር እንድሰደቱ ፈቀዱላቸው፡፡ እንድህም አሏቸው፡ (በሐበሻ ምድር እርሱ ዘንድ አንድም ሰው የማይበደል የሆነ ንጉስ አለ፡፡ አላህ ለናንተ አሁን ለአላችሁበት ችግር መፍትሄና መውጫ እስኪያደርግላችሁ ድረስ ወደሱ አገር ተጠጉ፡፡) ከዚያም ጥቂት ባልደረቦች ወደሐበሻ ምድር ወጡ፡፡ በምድሯም ሰፈሩ፡፡ በደግ አገርና ከመልካም ጎረቤት ጋርም መኖር ጀመሩ፡፡ ለሃይማኖታቸውም ሰላም አገኙ ጌታቸውንም መገዛት ቀጠሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ እያሉም የመካ ሰዎች እስልምናን ተቀበሉ የሚል ወሬ በሰሙ ጊዜ እንደገና ወደሀገራቸው ለመመለስ ወሰኑ፡፡ ከተመለሱም በኋላ ነገሩ እንደሰሙት ሳይሆን ቀርቶ እንደገና ስቃይ ማድረሱን የመካ ሰዎች በመቀጠላቸው አሁንም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ለሁለተኛ ጊዜ

ወደሐበሻ እድሰደቱ ፈቀዱላቸው፡፡ ይህህኛ ጉዞ የተመራው (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) በጃዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብ ነበር፡፡ የቁረይሽ ነገዶች እነሱ በዚያ ሐቀኛ ንገስ ምድር በጸጥታ፣ በክብርና በሙሉ መከታ እየኖሩ መሆኑን በሰሙ ጊዜ እነሱን እንደገና ወደመካ ለማስመለስ አሰቡ፡፡ መልክተኞቻቸውን ወደነጃሺ ላኩና እነሱን ለመልክተኛቸው እንደሰጥላቸው ጠየቁ፡፡ ነገር ግን እሱ እንዲህ አለ፡ ‹አይሆንም በአላህ ይሁንብኝ ወደአገሬ የተጠጉና ከሌሎች ግርብተና ይልቅ ጉርብትናዬን የመረጡ ሰዎችን ጠርቼ ሁኔታቸውን ሳልጠይቅ አሳልፌ አልሰጣቸውም፡፡›

ከዚያም (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ጃዕፈር ኢብ አቢ ጧሊብ የቁረይሽን መሰረተ ቢስ አባባልና ቅጥፈታቸውን ለመግለጽ ነጃሺ ፊት ቆሙ፡፡ እንድህም አሉ፡ ‹አንተ ንጉስ ሆይ! እኛ ጣዖታትን የምናመልክ፣ በክትን የምንበላ፣ እርም ነገሮችን የምንዳፈር፣ ዝሙት የምንፈጽም፣ ዝምድናን የምንቆርጥ፣ ጎረቤተን የምንጎዳና ከኛ ጉልበተኛው የደካማውን ገንዘብ የሚበላ ሰዎች ነበርን፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን አላህ ከኛ የሆነንና ዘሩን፣ እወነተኛነቱን፣ ታማኝነቱንና ጥብቅነቱን የምናውቀው የሆነን መልክተኛ ወደኛ ላከ፡፡ በአንድ አላህ አንድናምን፣ እሱንም እንድንገዛ፣ ከዚህ በፊት እኛና አባቶቻችን ከሱ ሌላ ያመልኳቸው ከነበሩ የድንጋዮችና ጣዖታት አምልኮ እንድንወገድ ጥሪ አደረገልን፡፡ እንድሁም እውነት እንድንናገር፣ አደራን እንድንመልስ፣ ዝምድናን እንድንቀጥል፣ የጉርብትናን መብት እንድናከብር፣ እርም የሆኑን ነገሮች ከመፈጸምና ደመን ከማፍሰስ እንድንታቀብ አዘዙን፡፡ ዝሙትን እንዳንፈጽም፣ በሀሰት እንዳንመሰክር፣ የሙት ልጅ ገንዘብን እንዳንበላና ጥብቅ ሴቶችንም ከዘለፍ ከለከለን፡፡ አንድ አላህን መንንም ያለማጋራት እንድናመልክ፣ ስገደትን እንድናደርሰ፣ ምጽዋትንም እንድንሰጥና ጾምንም እንድናደርስ አዘዘን፡፡ ሰይድና ጃዕፈር ሌሎችንም በርከታ የእስልምና ጉዳዮች ከቆጣጠሩለት በኋላ እንድህ አሉ፡ እኛም አመነው፣ በመልክተኝነቱም አመን፣ የመጠባቸውንም ነገሮች በመከተልን ምንንም ያለማጋራት አላህን ተገዛን፣ በኛ ላይ እርም ያደረጉትን ነገር ሁሉ እርም አደረግን፣ ለኛም የተፈቀደ ያደረገልንን ነገር ሁሉ የተፈቀደ አደረግን፡፡

በዚህ ተግባራችን ብቻ ወገኖቻችን፣ ጠሉን ስቃይም አደረሱብን፣ በሃይማኖታችንም ፈተና አደረሱብን፣ እንደገና አላህን ከመገዛት ይልቅ ሌላ ጣዖታትን ወደማምለክ እንድንመለስ፣ ፊት ስንሰራ ወደነበረው እርኩስ ነገሮችን የተፈቀዱ አደርገን እንድንፈጽም ሊያስገድዱን ሞከሩ፡፡ እነሱም በኛ ላይ ባየሉና በበደለን እንድሁም ባስቸገሩን፣ ከኛና ከእምነታችን መካከል ጣልቃ ለመግባት በሞከሩ ጊዜ ወደአንተ አገር ወጣን፣ ከሌሎችም አንተን መረጥንህ፣ ጉርብትናህንም ፈለግን፡፡ አንት ንጉስ ሆይ! አንተ ዘንድም አለመበደለን ተመኘን፡፡ ያን ጊዜ ነጃሺ እንድህ አላቸው፡፡ በመልክተኛው ላይ ከአላህ ዘንድ ከመጣው ነገር የምታውቀው ነገር አላህን? ሰይድና ጃዕፈርም አዎን አሉት፡፡ ነጃሺም አንብብለኝ አላቸው፡፡ አሳቸውም ከመርየም መዕራፍ የመጀመሪያውን ክፍል አነበቡለት፡፡ ነጃሺም ጺሙ እስኪርስ ድረስ አለቀሰ፡፡ የተነበበውን በሰሙ ጊዜ ቀሳውስትም አብረው አለቀሱ፡፡ በዚህን ጊዜ ነጃሺ እንድህ አለ፡ በአላህ ይሁንብኝ ይህ ቃል ዒሳ ከማጣው ብርሃን የወጣ ቃል ነው፡፡ ሂዱ በአላህ ይሁንብኝ እኔ እነሱን ለናንተ አሳልፌ አልሰጥም፡፡›

ወደሐበሻ ምድር የተደረጉ ሁለቱን ስደቶች ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው የጥንት ሙስሊሞች ስደት ከከህደት አገር ወደእምነት አገር የሚደረግ ስደት አለመሆኑን በግልጽ ሊገነዘብ ይችላል፡፡ ምክኒያቱም በመሰረቱ ስለሀገር መከላከል በሁሉም ላይ የተጣለ ግዴታ ስለሆነና ለበዳይም ሆነ ለጠላት አገርን ትቶ መሰደድ የተከለከለ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ያ ስደት ከፍርሃት አገር ወደሰላም አገር የተደረገ ስደት ነበር፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው የሐበሻው ንጉስ ነጃሺ በዚያን ጊዜ የእስልምና እምነትን የተከተለ ንጉስ አልነበረም የሚለው እውነት ሲሆን እሱ ሰዎች ለሃይማኖታቸው፣ ሕይወታቸውና ገንዘባቸው ደህንነት ሲሉ የሚጠጉበት ፍትሐዊ ንጉስ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ‹አላህ (ሱ.ወ.) በክህደት ላይ ቢሆንምኳ ፍትሃዊ አገርን ይረዳል በደለኛ አገርን የሙስሊም አገር ቢሆንምኳ ያዋርዳል› የተበላው፡፡

ስልጣን ከክህደት ጋር ሊዘልቅ የሚችል ሲሆን ከበደል ጋር ግን የሚቆይ አይሆንም፡፡ እንድሁም በዳይ አገር ገዢው ሙስሊምንኳን ቢሆን ዘላቂነት አይኖረውም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የፍትሃዊ ገዢ ደረጃ ከፍተኛ ቦታውም የላቀ መሆኑንና በትንሳኤም ቀን ምንም ዓይነት ጥላ በሌለበት አላህ በዙፋኑ ጥላ ከሚከልላቸው ሰባቱ ወገኖት ግንባር ቀደም እንደሚሆን አውስተዋል፡፡ ይህውም በፍትሃዊነቱ መላ ህብረተሰቡ የሚስተካከል እንድሁም በበደለኝነቱ መላ ማህበረሰቡ የሚበላሽ በመሆኑ ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) ለነብዩ ወደመዲና እንደሰደዱ በፈቀደ ጊዜ ከአላህ በሆነ ድል የታገዙ ሆነው ነበር የወጡት፡፡ ምክኒያቱም ይህ ጉዞ ሀገረን ለመገንባት አወንታዊ ሽግግር እንድሁም የመቻቻል ኑሮን፣ ወንድም ተማማችነትን እውን ለማድረግና ነብያችን ወደ ዓለም እንዲያደርሱ የታዘዙትን መልእክት በተሳካ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የሚያግዘውን አንድነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ስለነበር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

إِلاَّ {تَنصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ اللّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ الَّذِينَ كَفَرُواْ ثَانِيَ اثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِي الْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَاحِبِهِ لاَ تَحْزَنْ إِنَّ اللّهَ مَعَنَا فَأَنزَلَ اللّهُ سَكِينَتَهُ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُ بِجُنُودٍ لَّمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ الَّذِينَ كَفَرُواْ السُّفْلَى وَكَلِمَةُ اللّهِ هِيَ الْعُلْيَا وَ اللّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ} .

ትርጉሙም (((ነቢዩን) ባትረዱት እነዚያ የካዱት ሕዝቦች የሁለት (ሰዎች) ሁለተኛ ኾኖ (ከመካ) ባወጡት ጊዜ አላህ በእርግጥ ረድቶታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህም መረጋጋትን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያንም የካዱትን ሰዎች ቃል ዝቅተኛ አደረገ፡፡ የአላህም ቃል እርሷ ከፍተኛ ናት፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

በነብዩ ሂጅራ ስምንተኛ ዓመት አላህ (ዐ.ወ.) ለነብዩ መካ አልሙከረማን ግልጽ የሆነን መክፈት ከፈተላቸው፡፡ ሰዎችም ጭፍሮች ጭፍሮች እየሆኑ በአላህ ሃይማኖት ገቡ፡፡ በዚያን ጊዜ ጠባብና ውስን የነበረው የስደት ትርጉም ወሰን ወደሌለው ሰፊ ፍች የተሸጋገረ ሲሆን መላ የሕይወት አቅጣጫዎችን ሁሉ የሚያካትት ሆኗል፡፡ መካ ከተከፈተች በኋላ በድከመቱ ዘመን አስፈላጊ የነበረው ከአገር ወደአገር የሚደረገው ስደት ተቋርጧል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

إِنَّ الَّذِينَ تَوَفَّاهُمُ الْمَلَائِكَةُ ظَالِمِي أَنْفُسِهِمْ قَالُوا فِيمَ كُنْتُمْ قَالُوا كُنَّا مُسْتَضْعَفِينَ فِي الْأَرْضِ
قَالُوا أَلَمْ تَكُنْ أَرْضُ اللَّهِ وَاسِعَةً فَتُهَاجِرُوا فِيهَا فَأُولَئِكَ مَأْوَاهُمْ جَهَنَّمُ وَسَاءَتْ مَصِيرًا}

ትርጉሙም (እነዚያ (ለእምንት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ» አሏቸው፡፡ «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ፡፡ «የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን» አሉዋቸው፡፡ እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ በመመለሻነትም ከፋች!) ማለት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (ከመካ መከፈት በኋላ ስደት የለም፡፡ ነገር ግን ትጋድሎና ሀሳብ ነው ያለው፡፡) በማለታቸው የስደት መሰረተ ትርጉም ተለውጧል፡፡
በመካ እንባ ይኖር የነበረው ሰፍዋን ኢብን ኡመያ የተባለው ሰው እስልምና በገበበት ወቅት ያልተሰደደ ሰው እምነት የለውም ሲባል ሰማ፡፡ ወደመዲና ከመድረሴ በፊት እቤቴ አልገባም አለና ወደመዲና ሄደ፡፡ በዓባስ ኢብን አብደል ሙጠሊብ ቤት እንግድነት አረፈና ከዚያም ወደነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አመራ፡፡ አዚያ በደረሰም ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) (የዋህብ አባት ሆይ! ምን አግር ጣለህ? ) ሲሉ ጠየቁት፡፡ እሱም ያልተሰደደ ሰው እምነት የለውም ሲባል ሰለሰማሁ ነው አለ፡፡ ከዚያም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የዋህብ አባት ሆይ! ወደመካ ሜዳዎች ተመለስ በእምነታችሁም ጽኑ፡፡ ስደት በእርግጥ ተቋርጧል ነገር ግን ያለው ተጋድሎና ሀሳብ ብቻ ነው፡፡) አሉ፡፡
በሌላ ሐዲስም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (ሙስሊም ብሎ ማለት ሙስሊሞች ከምለሱና ከጁ ተንኮል የዳኑ የሆነው ሰውዬ ነው፡፡ ስደተኛ ማለትም አላህ የከለከለውን ነገር የተወ ሰው ነው፡፡) ከመካ ኢል ሙከረማህ ወደመዲና ኢል ሙነወራህ የሚደረገው የቦታ ቦታ ስደት በመካ መከፈት የተቋረጠ ቢሆንም ከፍተኛ ትርጉም ያላቸው በርከታ የስደት ዓይነቶች ዛሬም እንዳሉ ናቸው፡፡ እኛ አነሱን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እውነተኛ ስደት ማለት ወደተሻለና ጠቃሚነት ወዳለው ሁኔታ ለመሸጋገር የሚደረግ አወንታዊ ዝውውር መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ከስራፈትነትና ስንፍና ወደታታሪነትና ጥራት ወዳለው ሥራ፣ ከለኔባነትና ራስ ወዳድነት እንድሁም ከጭፍን ወገናዊነት ወደሰውችን ከራስ ማስቀደም፣ ወደወንድማዊ አጋዥነት፣ ወደእውነተኛ ሰብእነት, በብዝኃነት ወደማመን፣ የሰውን ልጅ ምርጫና የእምነት ነፃነት ወደማክበር መሸጋገር እውነተኛ የሃማኖት ስደት መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አረጋግጠዋል፡፡ እንድሁም የሰውን ልጅ በእምነት፣ በእውቀት፣ በእሳቦት፣ በስርኣት፣ በስነ ምግባር፣ በምጣኔ ሃብትና በማህበራዊ ዘርፍ ለመገንባት ጥረት ማድረግ ሀገረን የሚገነባ፣ ስልጣኔ የሚፈጥር፣ የማህበረሰቡን ጥቅምና የሰብኣዊ መብትን የሚያስከብር ትውልድ ለመፍጠር ያሚያስችል እውነተኛ ስደት መሆኑም ተጠቁሟል፡፡
የእውነተኛ ስደት ትክክለኛ ግንዛቤ ለዘላለም የማይቋረጠው የሃይማኖት ስደት ከድንቁርና ወደእውቀት፣ ከጥሜት ወደቅንነት፣ ከመጥፎ ጠባይ ወደመልካም ጠባይ፣

ከብልሹነት ወደአልሚነት መሸጋገር መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ይህም ሽግግር እውን በሚሆንበት ወቅት ስልጣኔን በመግንባትና ዓለምን በማልማት ረገድ ታላቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ሃማኖታችን መላ ዓለምን ወደማልማት እንድናመራ ያዘናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ብሏል፡

{هُوَ أَنْشَأَكُمْ مِنَ الأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا}

ትርጉሙም (እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡) ማለት ነው፡፡

የሙስሊሙ ህብረተሰብ የስንፍና ሳይሆን የሥራ ህዝብ፣ አፍራሽና አበላሽ ሳይሆን ገንቢ ህዝብ ሲሆን በዚህ የሰለጠነ ማህበረሰብ ዘንድ የኋላ ቀርነት ገጽታ በመንም ዓይነት መልኩ አይታይበትም፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ሙስሊም ሃማኖቱን ሊወድና በሱም ሊኮራ ይገባል፡፡ እንድሁም የሃይማኖቱን ደረጃ ከፍ ለማድረግና ከሰህተቶች፣ ወሰን ካለፈ ቃልና ከጸንፈኝነት በመራቅ የህገሩን ሉኣላዊነት ለማስከበር ጥረት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ እዚህ ላይ በተሳሳተ ሰንደቅ አላማ በሀሰተኛ ጂሃድ ስም ወደአሸባሪ ቡድኖች ከመጓዝና በህግም ሆነ በሃይማኖት ወደተከለከለው ውርደት አውራሽና አጥፊ ወደሆነው ህገ ወጥ ስደት ከማምራት መታቀብ ይኖርብናል እንላለን፡፡ የአንድ አገር ክብር እንደ አንድ ቤት ክብር ስለሆነ በአንድ ቤት ያለፈቃድ መግባት እንደተከለከለ ሁሉ ወደአንድ አገርም ህጋዊ ደንቦችን ያለማክበር መግባት የተከለከለ ነው፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንትም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

*        *        *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በስዲና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

በዚህ የተከበረ አጋጣሚ የሙሐረም ወር እርም ከሆኑ ወሮች አንደኛው መሆኑን ሳናስታውስ አናልፍም፡፡ በሱም በአጠቃላይ ጾምን ማብዛት የተወደደ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ብለዋል፡ (የግዴታ ከሆኑ ስግደቶች ቧላ እጅግ በላጩ ስግደት በማህል ሌሊት የሚሰገድ ሶላት ነው፡፡ ከሮመዳን ወር በኋላ በጣም በላጩ ጾም የአላህ ወር የሙሐረም ጾም ነው፡፡) በዚህ ወር በተለየ መልኩ የሚጾመው ቀን ደግሞ የዓሹራእ ቀን ነው፡፡ ነብያችን እንድህ ብለዋል፡ (የዓሹራእ ቀን ጾም አላህ በሱ ከሱ በፊት ያለውን ዓመት ወንጀል ያስተሰርያል ብዬ እገምታለሁ፡፡)ነብያችን ወደመዲና በመጡበት ጊዜ አይሁዳን የዓሹራእን ቀን ሲጾሙ አዩ እናም ስለምንድን ነው ብለው ጠየቁ፡ እነሱም ይህ የተባረከ ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን አላህ የእስራኢልን ልጆች

ከጠላታቸው ስላዳነ ሙሳ ጾሙት አሉ፡፡ ነብያችንም (እኔ ስለሙሳ ከናንተ ተቀዳሚ ነኝ) አሉና ጾሙት፡፡ ሰዎችም እንድጾሙት አዘዙ፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ኢብን ዓባስ የሚከተለውን አውርተዋል፡ (የአላህ መልክተኛ የዓሹራእን ቀን በጾሙና ሰዎችም እንድጾሙ ባዘዙበት ወቅት ሰዎች የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይህ ቀንኮ አይሁዳዊያንና ክርስቲያኖች የሚያከብሩት ቀን ነው አሏቸው እሳቸውም (የሚቀጥለው ዓመት ሲመጣ በአላህ ፈቃድ ሰጠነኛውን ቀን እንጾማለን፡፡) አሉ፡፡ ማለትም ዘጠነኛውን ቀን ከዓሥረኛው ቀን ጋር እንጾማለን ማለታቸው ነው፡፡ የዓሹራእን ቀን መጾም የተወደደ ሲሆን ተወዳጅነቱም ምሉእ የሚሆነው ዘጠነኛውንና ዐሥረኛውን ቀን በመጾም ነው፡፡

አላህ እሱ የሚወደውንና እሱን የሚያስደስተውን ሥራ እንዲያሳካልን፣ አደሱን የሂጅራ ኣመት የደገ፣ የበረከት፣ የድልና የብልጽግና ዓመት እንዲያደርግልን እሱኑ እንለምናለን፡፡ አሜን፡፡